ጌታችንና መድሃኒታችን የሕያው ቅዱስ አብ ቅዱስ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ በቅርቡ በእርሱ ለሚያምኑና እንደ ቃሉም እየኖሩ ላሉ ቅዱስ ሰዎች ብቻ ይመጣል፣ አስመሳዮችና እውነተኞች የሚለዩበት ሰዓት፣ እናንተ ግን የተወደዳችሁ ወንድሞቼ፣ ከልባችሁ ወደ ጌታ በመጮህ ይቅርታን ለምኑ፣ የበደሏችሁንም ይቅር በሉ፣ ከዚያም፥ የልጁ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻችኋል።

1 ተሰሎንቄ 4:16-17

ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤

ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።

ከኢየሱስ ጋር ወደ ገነት ደስታና ሰላም ወደሞላበት ፍቅርና መተሳሰብ ወዳለበት ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚወስደን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ የሆኑትንና በቃሉ ያሉትን ብቻ ከዓለም ውስጥ ለይቶ አውጥቶ ወደ አባቱ ይወስዳቸዋል፣ የመከራውንም ዘመን ያሳልፋቸዋል።

የቀራችሁ ብትሆኑም እንኳ፣ ስጋችሁን ቢልጡት አጋንንት፣ እጃችሁን ቢከትፉት፣ ነዳጅ ቢያፈሱባችሁ፣ መከራም ቢያጸኑባችሁ፣ አንገታችሁን ቢቆርጧችሁ፣ ሰይፍና መሮ ስለትም መጥረቢያ ቢያሳይዋችሁ፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያገኛችሁትን እምነት እንዳትለቁ እንዳትናወጡ፥ የጠራችሁ እርሱ ሕያው እግዚአብሔር የታመነ ነውና መንፈሳችሁና ነፍሳችሁን ያድናል በሥጋም የሚገድሏችሁን አትፍሩ ፥ ሥጋንና ነፍስን በአንድ ላይ መቅጣት የሚቻለውን እርሱን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት አብን ብቻ ፍሩ፣

አስታውሱ ይህ መከራ ለ7 አመት ብቻ ነው፣ የአውሬውን ምልክት 666ን ተቀብላችሁ ለዘለአለሙ በእሳት ባህር ከሰይጣን ጋር ከምትጣሉ፣ ለጥቂት ጊዜ መከራ በጸናባችሁ ጊዜ ብትታገሱ እናንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ሕይወትና ደም ብሩካን ጻድቃን ናችሁ፣ የአውሬውን ምልክት 666 በጭራሽ አትቀበሉ!!!፣ ኢየሱስም የዓለም ብርሃን የዘላለም ሕይወትን እንደገና ለዘላለም ይሰጣችኋል። በአጋንንት ትምህርት፣ በሀሰተኛ ጥምጥምና ካባ፣ በትእቢትም ሰዎችን በመከተል አትመሩ፣ እከሌና እከሌን፣ እነአባን፣ እነ እገሌ ፓስተርን አትከተሉ፣ ሁል ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጽኑ ዕለት ዕለትም አንብኑትም አሰላስሉትም አባታችን ጌታ እግዚአብሔር እንዳዘዘን። ሁሌም አይናችሁን የካህናት አለቃ የነገስታት ንጉስ ፍቅርና ቅዱስ ደግና መልካም እረኛ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ብቻ አድርጉ፣ የትኛውም ጻድቅ አያድናችሁም፣ ብቸኛው ስለኃጢአታችሁ የተሰዋው የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር በግ በመስቀል ላይ ስለናንተ ሞቶ ከሞትም በሦስተኛው ቀን የተነሣው የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻውን የዘለአለም ሕይወትን የሚሰጥ እርሱ ብቻ ነው! ንስሃ ግቡ፣ ይቅር በሉ፣ በየቤተ ክርስቲያኑ ለሀጢአት የምትሄዱ ሁሉ ንስሃ ግቡ፣ አመንዝሮች ሴሰኞች፣ አላጋጮች፣ አደንዛዥ እጽ ተጠቃሚዎች፣ አስመሳይ ጻድቃን መሳዮች፣ አስመሳይ አምላኪ መሳዮች፣ አስመሳይ ካህናት፣ አስመሳይ ዲያቆናት፣ አስመሳይ ፓስተሮች፣ አስመሳይ አስቀዳሾች፣ ጣኦት አምላኪዎች፣ ገንዘብ ወዳጆች፣ ዓለምን ወዳጆች ሁላችሁም፥  ልቡናንና ኩላሊትን እግዚአብሔር ይመረምራልና፣ እናንተ አሁን ከልባችሁ የሆነ እንባንና ጸጸትን አፍስሱ፣ አባታችን ኢየሱስ ፍቅርና ደግ ነውና እጆቹንም ከፍቶ እየጠበቃችሁ ነውና ንስሃ ግቡ፣ የንሰሃን ፍሬ አፍሩ፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ምሰሉ! አዱስ ሰው ሁኑ! ብዙ ሀሰተኛ ፓስተሮች፣ ብዙ ሀሰተኛ ጳጳሳት አስመሳዮች፣ ብዙ የጌታ አገልጋይ ነን ባዮች በሲኦል አሉ፣ ሁሉም ኢየሱስ ክርስቶስን አንቀበልም ብለው የሞቱ አሕዛብ በሲኦል እየነደዱ ናቸው፣ ስለዚህ ፌዙንና አስመሳይነቱን ትታችሁ ወደ እውነቱ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ተመለሱ! ሁላችሁም። እግዚአብሔር እንደ ዳዊት ከልቡ ንሰሃ የሚገባና በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ በቅድስና የጌታን ቃል እየጠበቃና እያደረገ የሚኖር ሰው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም የታጠበ ንጽሕናውንም ጠብቆ የሚኖር ሰው ይፈልጋል! ሃሌ ሉያ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ በቅድስና ያለነቀፋ ተገኝታችሁ የመከራውን ዘመን እንድታመልጡ አሁን ንቁ! ሃሌ ሉያ። እጆቹና እግሮቹ በቀራንዮ መስቀል ላይ በመሮ የተበሱት ስለናንተ ፍቅር ሲል ነው!! ማንም እውነትን አይውሰድባችሁ! በእናንተና በጌታ ፊት ማንም ገብቶ አያለያያችሁ! እጆቻችሁን አንስታችሁ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ታስፈልገኛለህ እኔ ራሴን ማዳን አልችልም ፥ የምታድነኝ አንተ ብቻ እንደሆንም ከቃልህ አምኛለሁ፥ አባቶቼ ሐዋርያት የሰበኩትም የእግዚአብሔር ልጅ በሆንም ባንተ እንዳምንና በእምነት ጽንቼ እንደቃልህ እንድኖር በአንተም ተጣብቄ መልካም ፍሬ በመንፈስ ቅዱስ እንዳፈራ ነው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ እኔን ለማዳን ስትል የእኔን ቦታ ሁሉ ወስደህ በእኔ ፈንታ ሆነህ ስለ ኃጢአቴ በመስቀል ላይ መሞትህን አምኛለሁ፥ ከሞትም በሦስተኛው ቀን አባትህ እግዚአብሔር አብ በመንፈስ ቅዱስ እንዳስነሣህ በልቤ አምኛለሁ፥ ጌታ ሆይ የበደሉኝን ሁሉ ይቅር ብዬአለሁ፥ ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ፥ በመስቀል ላይ በፈሰሰው ቅዱስ ደምህ መንፈሴን ነፍሴን ሥጋዬን ሁሉ አንጻኝ፥ በእኔ ውስጥ በልቤ ውስጥ አሁን ኑርልኝ ለዘላለሙም፥ ጌታ ሆይ ስላዳንከኝ ስለወደድከኝ በቁስልህ ስለፈወስከኝ

አመሰግንሃለሁ፥ ስሜን በሕይወት መጽሐፍህ ላይ ስለጻፍክልኝ አመሰግንሃለሁ፥ አሁን በአንተ በማመኔ ጌታዬና መድኃኒቴ ስላደረኩህ ሕይወትም ስለሆንከኝ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኜአለሁ፥ **ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው፤ አሜን ቅዱስ ሰማያዊ አባት ሆይ በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስላዳንከኝ አመሰግንሃለሁ እባርክሀማለሁ። ሃሌ ሉያ**

ወንድሞቼ ሆይ መጽሐፍ ቅዱስን ዕለት ዕለት አንብቡ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ከሆኑ በእግዚአብሔር በግ ደም ከታጠቡ ከቅዱሳንም ጋር ኅብረት አድርጉ። ከሁሉ በላይ እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችሁና ነፍሳችሁ ብርታታችሁም አፍቅሩ ውደዱ፥ ወደ ጌታ ጸልዩ፥ ወንድሞችንም ሁሉ ውደዱ፥ ለሚያሳድዱአችሁ ጸልዩ። ጌታ ሆይ ተባረክ ተመስገን ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን

የጌታችንና የመድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያው ዮሐንስ እንደጻፈው ምዕራፍ 14

1 ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ።

2 በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤

3 ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።

4 ወደምሄድበትም ታውቃላችሁ፥ መንገዱንም ታውቃላችሁ።

5 ቶማስም። ጌታ ሆይ፥ ወደምትሄድበት አናውቅም፤ እንዴትስ መንገዱን እናውቃለን? አለው።

6 ኢየሱስም። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።

1 ተሰሎንቄ 4

13 ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን።

14 ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና።

15 በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፤ እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም፤

16 ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤

17 ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።

18 ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።

1 ቆሮንቶስ 15

40 ደግሞ ሰማያዊ አካል አለ፥ ምድራዊም አካል አለ፤ ነገር ግን የሰማያዊ አካል ክብር ልዩ ነው፥ የምድራዊም አካል ክብር ልዩ ነው።

41 የፀሐይ ክብር አንድ ነው የጨረቃም ክብር ሌላ ነው የከዋክብትም ክብር ሌላ ነው፤ በክብር አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይለያልና።

42 የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል፥ ባለመበስበስ ይነሣል፤

43 በውርደት ይዘራል፥ በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል፥ በኃይል ይነሣል፤

44 ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፥ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ።

45 እንዲሁ ደግሞ። ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ።

46 ነገር ግን አስቀድሞ ፍጥረታዊው ቀጥሎም መንፈሳዊው ነው እንጂ መንፈሳዊው መጀመሪያ አይደለም።

47 የፊተኛው ሰው ከመሬት መሬታዊ ነው፤ ሁለተኛው ሰው ከሰማይ ነው።

48 መሬታዊው እንደ ሆነ መሬታውያን የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው፥ ሰማያዊው እንደ ሆነ ሰማያውያን የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው።

49 የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደ ለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን።

50 ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ይህን እላለሁ። ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፥ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም።

51-52 እነሆ፥ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበት ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን።

53 ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና።

54 ዳሩ ግን ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሲለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ፥ በዚያን ጊዜ። ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል።

55 ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መንሣትህ የት አለ?

56 የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው፤

57 ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።

58 ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ፥ የማትነቃነቁም፥ የጌታም ሥራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ።

**ራእይ 13-21።**

በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ የተባረከ የእግዚአብሔር አብ ባሪያ በመንፈስ ቅዱስ ተነድቶ ጻፈው።

ክብር ሁሉ ኃይልም ምስጋናም ባለጠግነትም ውዳሴም ለቅዱስ እግዚአብሔር፥ ከቡር አዳኝና መሢሕም ለሆነ ለእግዚአብሔር ቃል ለናዝሬቱ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ለቅዱስ መንፈሱም ይሁን አሜን።